ደስ ከማያሰኘው
የወደፊት ዝግጅት
በስተጀርባ

ደራሲ ጂ. ሙሬይ

በኤደንበርግ የስኮትላንድ ፍሪ ቸርች ጉባኤ ጡረታ የወጣ አገልጋይ (ቀጣይ)

ዘ ባነር አፍ ትሩዝ ትረስት

መግቢያ

በጣም ከታወቁ ቀደም ያሉ ምዕራባዊ ዝማሬዎች አንዱ የዊሊያም ኮውፐር “እግዚአብሔር በምስጢር ይሠራል፤ ድንቁንም ተግብሮ ያሳያል” የሚለው ነው፡፡ ኮውፐር ስሙ ከሃዘን እና ከድባቴ ጋር ተያይዞ የሚነሳ ዘማሪ ሲሆን፣ የክርስትናን ሕይወት የብርሃን ገጽታ ከማጣጣም ይልቅ ጸለምተኛ ጎኑን የበለጠ እንዳለፈበት የሚነገርለትም ሰው ነው፡፡ ስለዚህም ዝማሬው ከጥልቅ የሕይወት ተሞክሮው የወጣ እና የተደረሰም የተቀናበረም በመሆኑ በቀጣይ እንደተገለጹት ስንኞች ያሉ በውስጡ እጅግ ብዙ እውነቶቹን አምቆ ይዟል፡፡

ደስ ከማያሰኘው የወደፊት ዝግጅቴ በስተጀርባ

ርኅሩኅ ፈጣግታህን ደብቀሃል አባ፡፡

“ደስ የማያሰኝ የወደፊት ዝግጅት” ምን ማለት ነው? በክርስትና ሕይወት መጠበቅ ያለብን ይህን ነው ማለት ነው? እንዲያ ከሆነ ይህን የምንወጣው እንዴት ነው?

ልክ እንደእናንተ እኔም የዚህን አባባል ትርጉም ፈልጌ ነበር፡፡ ፈልጌ ካገኘኋቸው ነጥቦች ጥቂቶቹን በቀጣዮቹ ገጾች አካፍላችኋለሁ፡፡

ሀ. አስቀድሞ የታቀደ - ቅድመ-ዝግጅት (ፕሮቪደንስ) አለ

አስቀድሞ የታቀደ ጊዜው ያለፈበት ቃል ሲሆን፣ ለዘመናዊ ሰዎች ጆሮም እንግዳ የሆነ የደወል ድምጽ ነው። የሆነ ሆኖ ቃሉን ከፍታችሁ ስታዩት ትርጉሙ ግልጽ ይሆናል። “ቪዲዮ” የላቲን ቃል ሲሆን፣ “ማየት” የሚል ፍቺ አለው። እንዲሁም “ፕሮ” በላቲን “አስቀድሞ” የሚል ትርጓሜን ይሰጣል። በአንድነትም ቃሉ “ፕሮቪደንስ” “አስቀድሞ ማየት” የሚል ፍቺ አለው። በሕይወታችን አስቀድመን እናቅዳለን፤ ሊሆን ያለውን ግን ማየት አንችልም። እግዚአብሔር ለፍጥረቱ ሁሉ እቅድ አዘጋጅቷል። እርሱ ሉዓላዊ አምላክ ስለሆነ ሁሉም ነገር እንደ እቅዱ ይሆንለታል። የወደፊት እቅድ የእግዚአብሔር አስደናቂ ሥራ ነው፤ በዚህ እቅዱ መሠረትም ነው በአጽናፈ ዓለሙ ላይ ሁሉም ነገር በልቡ ውስጥ እንዳለው እየፈጸመው ያለው።

በዌስትሚኒስትር ጉባኤ የእምነት አንቀጽ ላይ “እግዚአብሔርን ለሚፈሩ እንደ አሳቡም ለተጠሩ ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን” የሚለው መንፈሳዊ ቀኖና በግልጽ የተቀመጠው የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ሥርዓት ሆኖ ነው፦

> የዘላለም ሁሉ አምላክ እግዚአብሔር፣ እጅግ በላቀ ጥበቡ እና በፈቃዱ ቅዱስ ምክር፣ በነጻነት እና ባለመናወጥ ሁሉን አስቀድሞ ወስኗል፤ ሆኖም እርሱ መሠረቱ የማይነቃነቅ እንጂ የኃጢአት ደራሲ ወይም አመጻ የፍጥረት ፈቃድ ይሆን ዘንድ ያቀረበ፣ ወይም እርሱ ፍጥረቱ የፈጠረው ግሳንግስ ፍጥረታዊ ነጻ መውጫ አይደለም። (ምዕራፍ 3፣ ገጽ 1)

አጭሩ ካቴኪሲዝም እንዲህ ብሎ ይጠይቃል፦ “እግዚአብሔር ሥርዓቱን የሚፈጽመው እንዴት ነው?” መላሹም ይመልስለታል፦ “እግዚአብሔር ሥራውን የሚፈጽመው በፍጥረት ሥራው እና በእቅዱ መሠረት ነው።” (ጥያቄ 8) የቤዛነቱስ ጉዳይ? እርሱም በወደፊት እቅዱ ውስጥ ተካቷል! ይህም ታላቅ የወደፊት እቅዱ ነው።

እግዚአብሔር ይህንንም እቅዱን ይዞ ልጁን ወደ ዓለም ሲልከው፣ ለሰው ልጆች - ለሕዝቦች ቤዛ እንዲሆን ነው። ሲያል የሚገባቸውን ኃጢአተኞች ለማዳን ወስኖ፣ ዓለም ሳይፈጠር በክርስቶስ ኢየሱስ መረጣቸው። አስቀድሞ እንደመረጣቸው ያወቁ ታዲያ “የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ እንደወሰነ” ያምናሉ። ከዘላለም እስከዘላለም ለምትዘረጋው ቤተ ክርስቲያኑ እግዚብሔር እቅድ አለው።

ከዚህ ታላቅ ዓላማው ጋር በተያያዘም፣ ቶማስ ቦስተን እንደሚለው “እግዚአብሔር፣ በዘላለማዊ ሥርዓቱ እንደ ነሐስ ተራሮች የማይነቃነቅ እና የማይናወጥ አድርጎ የእያንዳንዱን ሰው እጣ ወስኗል፤ በዚያም የጠማማው እና የቀናው እንደየዓይነቱ አስቀምጧል። ኢዮብ በዚያ መከራው መሐል እንዲህ ብሏል፦ “በእኔ ላይ የተወሰነውን ይፈጽማል፤”

የእግዚአብሔር እቅድ በሕይወቴ በዝርዝር ይተነተናል። ስለዚህም ብዙ ነገር ሊባል ይችላል፦

1ኛ. እቅዱ ፍጹም ነው፤ እግዚብሔር የሚያደርገው ሁሉ ፍጹም ነው፡፡ ለእኔ ለጊዜው ፍጹም ላይመስለኝ ይችላል፤ ነገር ግን፣ በፍጻሜው ወደታላቅ የእግዚአብሔር ክብር ይወስዳል፡፡

2ኛ. እቅዱ ጠቅላይ ነው፤ ሁሉን ይጠቅላል፡፡ የሚተገበረው የሚደረገው ሁሉ በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር ሆኖ ነው፡፡ ይህም ጥቃቅኗን ነገር ሳይቀር የሚመለከት ነው፡፡ “የእናንተስ የራሳችሁ ጠጉር ሁሉ እንኳ ተቆጥሯል” (ማቴ. 10፡30)፡፡

3ኛ. እቅዱ ለእኔ ለዘለቄታው ለበጎ ነው፤ እግዚአብሔርን ለሚፈሩ ሁሉ እንደ አሳቡም ለተጠሩ “ነገር ሁሉ ለበጎ እንደሚደረግ” የራሱ የእግዚአብሔር ዋስትና አላቸው (ሮሜ. 8፡28)፡፡ እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመኛል? ተቃዋሚዬ እዚህ ግባ አይባልም፡፡ የቸሩ እግዚአብሔር የሕይወቴ ዓላማ በእርግጥ ይፈጸማል፡፡

4ኛ. እቅዱ ምስጢር ነው፤ እርሱ የእቅዱ ሁሉ አርቃቂ በመሆኑ ወደፊት ምን እንደሚሆን የሚያውቀውም እርሱ ብቻ ነው፡፡ የሕይወቴ ዝርዝር ጉዳይ እኔ ከመወለዴ በፊት ተጽፏል፡፡ ሆኖም በሕይወቴ እስኪፈጸም ድረስ እግዚአብሔር ይሰውረዋል፡፡ እኔ በሕይወቴ ሆኖ የማየው በየእለቱ እርሱ የሰወረውን ሲገልጠው ነው፡፡ ይህ የእርሱ ሃሳብ ምስጢር መገለጡም ለሕይወቴ በጎ ነው፡፡

እግዚአብሔር አንድ ፈቃድ ቢኖረውም፣ የተሰወረ ፈቃድ እና የተገለጠ ፈቃዱንም እንናገራለን፡፡ የተገለጠ ፈቃዱ በቃሉ የሚነበብ በመሆኑ የተግባራችን ሕግ ነው፡፡ የተሰወረ ፈቃዱ ግን በዘላለም እቅዱ የሚታወቅ እና ሲገለጥ የሚታይ ነው፡፡

ይህ ትምህርት በግልጽ በቶማስ ቦስተን ቃሎች ውስጥ በግልጽ ተቀምጧል፡-

> *“ከእግዚአብሔር ጋር የሚራመድ የቃሉ ተመልካቾች እንዳሉት እና እግዚአብሔር ለሕዝቡ ራሱን በተለየ መንገድ የሚገልጥበት ዘላለማዊ እቅድ እንዳለው ሊረዳ ይገባል፡፡ በአንዱ ሲናገረን ስናይ፣ በሌላው ደግሞ ፈጽሞት እናገኘዋለን፡፡ እነዚህን ሁለት መጻሕፍት እያንዳንዱ የቅድስና ተማሪ ሊያውቃቸው ይገባል፡፡ እነዚህ ሁለቱም በአንድ እጅ እንደመጻፋቸው፣ በጥንቃቄ መነበብ ያለባቸው የሃይማኖት ሰም ባላቸው ብቻ ሳይሆን በባለእሴቶቹም ነው፡፡ እነዚህ በጋራ ሲጠኑ አንዱ ለአንዱ ብርሃን የሚሰጥበትን ጸጋ ያገኛል፤ ስለዚህም ቃሉን ማንበብ ተግባራችን እንደሆነ ሁሉ፣ የእግዚአብሔርንም ሥራ መመልከታችን ተግባራችን ይሆናል፡፡”*

ስብከቱ የተወሰደው ከመዝሙር 107፡43 ነው፡- “ጠበበኛ የሆነ እና ይህን የሚጠብቅ ማን ነው? እርሱ የእግዚአብሔርን ምሕረት ያስተውላል፡፡” “ይህንን የመጠበቅ” ተግባራችንን መወጣት ካለብን፣ የሚያስፈልገን መሥፈርት ማስተዋል ነው፤ ይሁንና በዚህ ውስጥ የእግዚአብሔርንም ርኅራኄ እና ፍቅር እናተርፋለን፡፡ የሰው ልጅ ከእኛ አንጻር እንደ ባሕርዩ ወይም እንደ ባሕርዩዋ እንዴት እንደሚቆም

እናውቃለን፡፡ እግዚአብሔር ስለልጆቹ ስላለው አቋም ስናጠና የምናገኘው ፍቅሩን ነው፡፡ ወደፊት እቅድ የራሱ የሆነ ቋንቋ አለው፡፡

የተለያዩ ዓይነቶች የወደፊት እቅዶች አሉ፡፡ እንደ ተዓምራት ያሉ ያልተለመዱ የወደፊት እቅዶች አሉ፤ እንዲሁም የተለመዱ የምንላቸው እንደ አረስራሽ ዝናብ ያሉ የወደፊት እቅዶችም አሉ፡፡ ቀይ ባሕርን እንደመሻገር ያሉ ታላላቅ የወደፊት እቅዶችም አሉ፤ ልክ የንጉሡን እንቅልፍ እንደማጥፋት ያሉ የወደፊት እቅዶችም አሉ፡፡ የምንወዳቸው ወይም ፈገግ የሚያሰኙ የወደፊት እቅዶች አሉ፤ ደግሞም እንደመስቀል ሞት ያሉ ደስ የማያሰኙ ጨለምተኛ ሆነው የሚገለጡም የወደፊት እቅዶች አሉ፡፡

ደስ የማያሰኙ የወደፊት እቅዶች ከዚያው ከምንወዳቸው እና ፈገግታን ፈጣሪ የወደፊት እቅዶችን ከሚሰጠን ከአንዱ አባት የሚወጡ ከሆነ፣ ሁለቱን እንዴት ማስታረቅ ይቻላል? እግዚአብሔር በእኛ ሕይወት የሚሠራባቸውን መንገዶች በመረዳት ልናጸድቅ የምንችለውስ እንዴት ነው?

ለ. ጨለምተኛ የወደፊት እቅዶች አሉ

በሕይወታችንም ሆነ በአጽናፈ-ዓለሙ የጨለማ የወደፊት እቅድ መኖሩን በጆን ፍላቨል አባባል “የወደፊት እቅድ ምስጢር” ነው፡፡ ሰባኪው ቶማስ ቦስተንም በመክብብ 7፡13 ላይ በሰበከው ተከታታይ ስብከቶቹ ይህንኑ ችግር ዳሶታል፡፡ “የእግዚአብሔርን ሥራ ተመልከት፤ እርሱ ጠማማ ያደረገውን ማን ሊያቀናው ይችላል?” “ዘ ክሩክ ኢን ዘ ሎት” በሚል ርዕስ እርሱ ካለፈ በኋላ ታትሟል፡፡

ተቃውሞ በሕይወታችን ሲመጣ ከሁለቱ በአንዱን መንገድ ምላሽ እንሰጣለን፡፡ ይህ ከእግዚአብሔር የመጣ አይደለም፤ ስለዚህ የእግዚአብሔርን እቅድ ሊያቆመው አይችልም እንላለን፤ ወይም ይህ ነገር እግዚአብሔር በእኛ ላይ መቆጣቱን ያመላክታል የሚል ድምዳሜ ላይ እንደርሳለን፡፡ በሁለቱም የአባታችንን ባሕርይ ዝቅ የማድረግ ወንጀል የምንሠራ ሲሆን፣ በዚህም የእኛን ባሕርያዊ መገለጫ ከእርሱ ጋር በማጣጋት በሥራው ላይ መስተጓጎል እንፈጥራለን፡፡ “የሕመም ፈጣሪ ክስተቶች ትክክለኛ ምልከታ” ቦስተን በጽሑፉ መንደርደሪያ እንደሚለው “በጥቅሉ ለክርስቲያን ከሥሩ ተደላድሎ እንደመቆሚያ መኖሩ አስፈላጊ ነው፡፡” ቦስተን ሃሳቡን በመቀጠልም፣ “ያም ሃሳብ የሚገኘው ሰብዓዊ ስሜትን ተጠቅሞ ሳይሆን በእምነት ብቻ ነው፤ ምክንያቱም የነገሩን ውስጠ-ነገር በትክክል የሚወክለው የቃሉ ብርሃን ነው፤ በክስተቱ ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔርን ሥራ መርምሮ የሚያስረዳውም ይኸው ነው፤ በውጤቱም የታለመው ነገር የእግዚአብሔርን ፍጽምና ያሳያል፡፡”

ክርስቲያን በፍጹም አቋሙ ቁመና እንኳን ቢሆን የቆመው በኃጢአት በወደቀች ዓለም ውስጥ ነው፡፡ ስለዚህም በሥጋ ውድቀት ምክንያት የተከተለው ሕመም ምክንያት ሁሉ ሊያመው ይችላል፡፡ ከቀደመ

ኃጢአቱ ጋር ተያይዞ የሚመጡ አስከትሎቶች ሕይወቱን ሊያውኩ ይችላሉ፡፡ በሰማይ አባቱም ሊቀጣ ይችላል፡፡ የሰይጣንም የጥቃት ቀስቱ ማነጣጠሪያ መሆኑ መዘንጋት የለበትም፡፡ በሰይጣን ቁጥጥር ሥር ያለችውም ዓለም በክርስቲያን ላይ ጨካኝ ነች፡፡ ስለዚህም የመከራዎቹ ሁሉ ማሠሪያው ክርስቲያን መሆኑ ነው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳስጠነቀቀው “በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ” ብሎ ነው (ዮሐ. 16፡33)፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ሳያወላውል እንደሚነግረን መከራ የእውነተኛ ክርስቲያን መደበኛ የሕይወቱ አንድ ክፍል ነው፡፡ ዕብራውያን ምዕራፍ 11 በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔርን የተከተሉ ሰዎችን የመከራ ምስክሮች አድርጎ አቅርቧቸዋል፡፡ አዲስ ኪዳን ደግሞ “በመከራ ፍጹም ስለመደረግ” ታላቅ ምሳሌ ያቀርብልናል (ዕብ. 2፡10)፡፡ ብዙ አማኞችም የክርስቶስ መከራ ተካፋዮች ስለመሆናቸው ይነግረናል (1ኛ (ጴጥ. 4፡13)፡፡ የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን የትምህርቷ ሁሉ ማዕከል “በመከራ ሃሴት ማድረግ” ነበር፡፡ “ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል…” (ሐዋ. 14፡22)፡፡

በዌስትሚኒስትር ጉባኤ የእምነት አንቀጽ የወደፊት እቅድን አስመልክቶ በሕግ-ነክ ቃላት የተቀነበበ ምዕራፍ ያለው ሲሆን ያም እግዚአብሔር ከልጆቹ ጋር ባለው ግንኙነት ላይ አተኩሯል፡፡

> እጅግ ጥበብን የተሞላው፣ ጻድቅ እና ቸር የሆነው እግዚአብሔር፣ አንዳንድ ጊዜ ልጆቹን በፈተና ውስጥ እንዲያልፉ ይፈቅዳል፤ በዚያም የልባቸው ከጉድፍ ለማጥራት፣ ስላለፈው ኃጢአታቸው ለመገሰጽ፣ ወይም በልባቸው ያለውን የጠነከረ እና የተደበቀ አታላይ እና ወላዋይ ማንነት ለመስበር እና ትሁታን ለማድረግ፤ ሳያቋርጡ ለእርሱ ቅርብ እንዲሆኑ እና ለእርዳታቸው በእርሱም ላይ እንዲደገፉ ለማድረግ እንዲሁም ከፊታቸው ሊከሰት ባለ ኃጢአት ላይ ንቁ እንዲሆኑ ቅዱሳን እና ንጹሃን እና ቅዱሳን ሆነው መንገዳቸውን እንዲፈጽሙ ነው፡፡

በሚያሳዝን ሁኔታ ግን እንዲህ ያለው ትምህርት እና ምልከታ ከብዙ የዛሬዋ ቤተክርስቲያን ክበብ ውስጥ ተወግዷል፡፡ ይህም በምልከታ የክርስትና ሕይወት ዋነኛ ዓላማ መዝናናት እና ደስታ እንደሆነ አመላካች ነው፡፡ ከዚህ በተቃርኖ የሚመጣ ነገር ሁሉ ተገፍቶ የሚወገድ ነው፡፡ ምክንያቱም የዘመኑ ክርስቲያን የሚፈልገው ከችግር-ነጻ የሆነን ክርስትና ነው፡፡ የወንጌል ጤና፣ ሐብት እና ስኬት ለመስክ ጉብኝት ወጣ ብሏል፡፡ እንደክፉ እድል ሆኖ፣ የዚህ አመለካከት ባዶነት መከራ ወይም ኃዘን ሲመጣ ይጋለጣል፡፡ ስለዚህም እምነታችን በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት እንዳለበት ግልጽ ሆኖ ይታያል፡፡

ሐ. በጨለማ የወደፊት እቅድ - አቅርቦት ውስጥ የእግዚአብሔር ንድፍ

የፈተና ወይም የጨለማ አቅርቦት የክርስትና መንገዶች መሆናቸውን ካየን፣ አሁን ደግሞ ዓላማቸው ምን እንደሆነ መመርመር አለብን፡፡ እግዚአብሔር ወደ ሕይወታችን ከሚያመጣቸው ነገሮች ጋር ተያይዞ በአመጽ እና በቁጣ ምላሽ መስጠት ኃጢአት መሆኑ እንዳለ ሆኖ፣ እነዚህ ነገሮች ለምን የእጣ ፈንታችን ክፍሎች እንደሆኑ ማሰብ ግን ትክክል ነው፡፡ ትክክል ነው አይደለም የሚለውን መጠየቂያ መንገድ አለ፡- “ለምን?” በሚል ጥያቄ እግዚአብሔር እየሠራ ስላለው ነገር ሃሳብ እንሰጥበታለን፡፡ በእነዚህ ደስ በማያሰኙ ተሞክሮዎች እግዚአብሔር በሕይወታችን ሊሠራ ያሰበው ነገር ምንድነው? እግዚአብሔር በመከራዎቻችን ከሚሠራቸው ንድፎች ጥቂቶቹ ቀጥሎ ተመልክተዋል፤

ነኛ. መከራ የእኛን አቋም ለመለየት ይመጣሉ

“በእጣ ውስጥ ያለ ጥመት” ቦስተን እንደሚለው “ሰዎች ወደእውነተኛ ቀለማቸው እንዲመጡ የሚያደርግ ታላቅ አቅርቦት ነው”፡፡ ሲ.ኤስ.ሊዊስ በአንድ ወቅት እንዳሉትም “መከራ ክርስቲያን ወደ ሲያል ከሜድ ለማገድ የገባ መንገድ መዘጊያ ነው፡፡” አንድሪው ፉለር ደግሞ “በረዶውን የምታቀልጠው የቀትር ጸሐይ ሸክላውን ግን ታጠነክረዋለች፡፡” ይላል፡፡ አንድሪው ሃሳቡን በመቀጠልም “መከራ አንዳንዱን ሲያጠራው አንዳንዱን ደግሞ ይውጣዋል” ብሏል፡፡ የአንድ ሰው የክርስትና ሕይወት መፈተን ልክ በማዕበል እንደተመታች መርከብ መሆን ነው፤ ወይም አንድ ቤት በብርቱ ነፋስ ከመመታቱ ጋር ይመሳሰላል፡፡

ስምዖን ጴጥሮስ እንደጻፈልን የክርስቲያን እምነት ተግዳሮት ያለበት እና የተፈተነ ነው (ነኛ ጴጥ. ነ፡3-7)፡፡ ይህም የእምነታችንን ትክክለኝነት የሚያሳይ ነው፡፡ ሐዋርያው ጴጥሮስ በጊዜው ለነበሩ ክርስቲያኖች ምንም እንኳ የጊዜው መከራቸው ብዙ ቢሆንም፣ ታላቅ ተስፋ እንዳላቸው ጽፏል፡፡ ምክንያቱም ከመከራቸውም በስቲያ እግዚአብሔር እንደወርቅ አንጥረኛ በሥፍራው ያለ መሆኑ ነው፡፡ እንደ ወርቅ የጠራውን ከሰው ውስጥ በእርሱ ላይ የሚተማመንን ሌላ ማንነት ማውጣት ይፈልጋል፡፡ በራስ-የመተማመን ቁሻሻ ተገፍቶ ሲወጣ፣ እምነት ለክርስቶስ ኢየሱስ ምስጋናን እና ክብርን ያመጣል፡፡

አብርሃም የእምነት ሰው በመሆኑ የእምነትን ፈተናዎች ታግሶ አልፏል፡፡ አብርሃም በዑር የነበረውን ምቹ ሕይወት ነው እግዚአብሔር እንዲተው እና እርሱ ወደሚያሳየው የተስፋ ምድር እንዲሄድ፣ በዚያም ዘሩን እንደሚያበዛለት ነበር የነገረው፡፡ ይሁን እንጂ በዓመታት ሂደት የተስፋ ቃሉ በፍጹም የማይፈጸሙ መስለውም ነበር፡፡ የአብርሃምን የማንነት ውርስ የሚወርስ ስለማግኘቱ ምንም ፍንጭ አልነበረውም፡፡ ስለዚህም አብርሃም በትዕግስት ማጣት ምክንያት በራሱ መንገድ ልጅ ለማግኘት ጥሮ ነበር፡፡ በውጤቱም ከግብጻዊቱ አጋር እስማኤልን አግኝቷል፤ እግዚአብሔር ግን እናትና ልጁን በተስፋ ቃል ኪዳን ውስጥ

የሌሉ በመሆኑ ከአብርሃም ሕይወት እንዲወጡ አዞታል። ከዐሥራ አንድ ዓመት በኋላ የተስፋው ቃል ልጅ ይስሓቅ ተወለደ። ይስሐቅም በመሰዊያ ላይ መቅረብ ነበረበት። እግዚአብሔርም ይስሐቅን በመሰዊያው ላይ እስካገኘ ድረስ፣ የአብርሐም የሆነው ሁሉ የእርሱ እንደሆነ አልተቀበለም። ይስሐቅ በቀረበለት ጊዜ ግን እግዚአብሔር በአብርሐም እምነት ተደንቆ፣ "አንድ ልጅህን ለእኔ አልከለከልህምና እግዚአብሔርን የምትፈራ እንደሆንህ አሁን አውቄአለሁ..." አለው። አብርሃም እምነቱ ተፈተነ፤ እምነቱም እንደ ንጹሕ ወርቅ ሆኖ ታየ፤

"በእሳት ፈተና ውስጥ መንገድ ባለፍክ ጊዜ፣

ጸጋዬ ዋስህ ነው ግቤ ለማድረሴ፤

ያነደድኩት እሳት እኔ የነደፍኩት፣

አይጎዳህም እና አይግባብህ ስጋት፤

የእሳቱ መንደድ ጉድፍን ማስወገድ ነው፤

ማንነትህ ጠርቶ ንጹህ ወርቅ ሊያረገው።

2ኛ. መከራ ኃጢአታችንን አውጥቶ እንደ ስጥ ያሰጣዋል - ይገልጠዋል

በክርስትና መንገድ ላይ ስንጓዝ የራሳችንን እውነተኛ ማንነት በትክክል እንደማናውቀው እንረዳለን። የልባችንን አታላይነት እንኳ ሳናውቀው ጭምር በክርስትና አገልግሎት ላይ ልንሰማራ እንችላለን። ዶክተር ሎይድ-ጆንስ እንዳለው "ራሳችንን በጣም በጎ ሰው እንደሆነ አድርገን እንቆጥረዋለን፤... ሆኖም ስለአብዋራ እና ስለአመድ ብዙ አንረዳም።" በጸጋ እና በእምነት ስለማደግ አበክረን እንጸልያለን፤ የእግዚአብሔር መልስ የሚመጣው ግን ባልገመትነው መንገድ ነው። ጆን ኒውተን ይህን ሕመም የተሞላውን ግኝት ስለማግኘቱ እንዲህ ገልጾታል፡-

"እግዚአብሔር በጸጋ፣ በፍቅርና በእምነት

እኔን እንዲያሳድግ በጸሎት ጠይቅኹት፤

ስለጌታ ማዳን በብዙ፣ በጥልቀት፣

እንዲያበራልኝም ጌታ የጌታን ፊት፣

ተግቼ፣ ማልጄ፣ አብዝቼ ፈለግኹት።

የጸሎትን ጉልበት ያሳወቀኝ ጌታ፣

“እመን ብቻ…” ብሎ ቋጠሮ የሚፈታ፣

የመጣበት መንገድ ጸሎቴን ሊመልስ፣

ተስፋ የሚያስቆርጥ ነው ልብን የሚመልስ፤

ጠብቄ የነበረው በጊዜዬ እንዲደርስ፣

በጸሎቴ ፍጥነት ወዲያው እንዲመራ፣

ነበር በእኔ ጊዜ ጌታ እንዲሠራ፣

በፍቅሩ ጉልበት፣ በጉልበቱ ጽናት፣

ኃጢአቴን ረትቶ እንዲሰጠኝ እረፍት፣

ወድጀ ነበረ፣ ቢሆን በእኔ ምኞት።።

ግና በዚያ ፋንታ፣ ልቤን አወረደው፣

ድብቁን ክፋቴን በልቤ ገለጠው፤

የሲያል ቅጥረኞች፣ የክፉው መላዕክት፣

እስኪያላግጡብኝ በየደረስኩበት፣

የእኔ ዝቅ ማለት መወርወሬ መሬት፣

መልስ ሆኖ አገኘሁት እኔ ለጸለይኩት።።

ሮበርት ሙሬ ማክቼኒ የታወቀ ማንኛውም ኃጢአት ዘር መገኛ ሥፍራው ልቡ እንደሆነ ተናግሯል።። በልብ ውስጥ ያለ አለመታመን ምን ያክል እምቅ አቅም አለው ይሆን!? እኛ ልክ እንደ ፔትሮልየም ማበልጸጊያ ተቋም ነን።። ፈንድቶ ብዙ ጥፋት ለማድረስ ቅጽበት ብቻ ይበቃናል።። በብዙ ቅዱሳን ሕይወት የፈነዱ ኃጢአቶች ምን ጥፋት እንዳደረሱ እስቲ መለስ ብላችሁ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ተመልከቱ።። የአብርሃምን መታለል፣ የኢዮብን ያልተገሩ ቃላት፣ የሙሴን ብስጭት፣ የአሳፍን ዥዋዥዌምረም እና

የጳውሎስን ኩራት.... ተመልከቱ፡፡ ኢዮብ በኋላ ላይ እንዲህ ማለት ችሏል፡- “... ስለዚህም ራሴን እንቃለሁ፤ በአፈርና በአመድ ላይ ተቀምጬ እጸጸታለሁ” (ኢዮ. 42፡6)፡፡ አሳፍም ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ “እኔ የተናቅሁ ነኝ፤ አላውቅሁምም...” (ወይም በእኔ አረዳድ በፊትህ እንዴት ሞኝ እና አላዋቂ ነበርኩ!) ብሏል (መዝ. 73፡22)፡፡

እንዲህ ያሉ የሕይወት ግኝቶች ስለራሳችን ዝቅ አድርገን እንድናስብ፤ እና ስለክርስቶስ ኢየሱስ አብዝተን እንድናስብ ያደርጉናል፡፡ ስለኃጢአታችንም ለየት ባለ አዲስ ጥልቀት እንድንጸጸት እና የኃጢአተኝነታችንን እውነተኛ ገጽታ በጠራ መነጽር እንድናይ ያደርጋሉ፡፡

3ኛ. መከራ የሚመጣው ባሕርያችንን ለማነጽ ነው

ሌላ ምንም ሊኖረን ይችላል፣ ባሕርያችን እንደሚገባው ያልታነጸ ከሆነ፣ ምንም እንደሌለን ይቆጠራል፡፡ የውድቀቶች ሁሉ ቁንጮ ባሕርይን ከማነጽ መውደቅ ነው፡፡ በተለመደው ሕይወትም ቢሆን ባሕርይ የሚታነጸው ችግሮችን ታልፎ እና አሸንፎ ነው፡፡ ዛሬ የምንኖርበት ማኅበረሰብ ባሕርይን በማነጽ ተቃራኒ የቆመና በተቃራኒው የሚታገል ነው፡፡ በቤተክርስቲያንም ቢሆን ወጣቶች እና ታዳጊዎች ባሕርይን በማነጽ ረገድ ምሳሌ የሚሆናቸው የለም፡፡ ስለዚህም ብዙዎቹ በአካል አድገውም ቢሆን ታዲያ መንፈሳዊ ሕጻናት ሆነው ቢታዩ አይገርምም፡፡

አንድ ታዋቂ አትሌት አሸንፎ ወርቅ ሲያጠልቅ እናያለን፡፡ በውድድሩ እለት ሲታይ ነገሮችን ቀለል አድርጎ እንዳሸነፈ ብናየውም፣ ሕመም ከተሞላው ልምምድ እና አስቸጋሪ ከሆኑት ተቀናቃኞቹ የገጠመውን ፈተና ተወጥቶ እንደሆነ ግን መዘንጋት የለብንም፡፡ እግዚአብሔር ባሕርይን የሚያንጽበት መንገድ በሮሜ 5፡1-5 ተገልጾአል፡- “...በመከራችን ደግሞ እንመካለን” ይላል፡፡ “መከራ” የሚለው የግሪክ ቃል “መጭመቅ” ከሚለው ግሥ የመጣ ነው፡፡ መጭመቅ ወይን ጨምቆ የወይንን ጠጅ እና ወይራን ጨምቆ ለወይራ ዘይት ለማዘጋጀት ከሚውለው ቃል ጋር የተቆራኘ ነው፡፡ ቃሉ የውጫዊውን የመከራ ተጽዕኖ እና የውስጣዊ ስቃይን ልኬታ ገላጭ ነው፡፡ መከራ ትዕግስትን ያደርጋል - ያንጽዋል፡፡ ይህም ከአንድ ነገር ጋር መጽናትን እና ከዚያም አለመለየትን አመልካች ነው፡፡ ጀግንነት የተሞላው ይህም ጽናት - ትዕግስት የ1954ቱ ትርጉም እንደሚለው “ፈተናን” ያደርጋል - ይሠራዋል፡፡ ይህ ቃል ግን በትክክል ወክሎ የቆመው “ባሕርይ” የሚለውን ሃሳብ ነው፡፡ ከመከራ ሂደት በስቲያ የሚታነጽን ባሕርይ ማለት ነው፡፡

እግዚአብሔር ያለመከራ ባሕርይን አያንጽም ወይ የሚል ጥያቄ ሊኖረን ይችላል፡፡ ይህ መላምታዊ ጥያቄ ነው፡፡ እርሱ ምርጫውን ያደረገው በዚያ መንገድ መሥራትን ነው፡፡ ወጣቱ ዮሴፍ ነገሩ ሁሉ እንደጠፋ የሚታሰብበት ሁኔታ ላይ ገብቶ ነበር፡፡ እርሱ ከነበረበት የባርነት ሕይወት አንጻር ወደ መሪነት ይመጣል ብሎ መገመት የማይቻልበት ሁኔታ ላይ ነበር፡፡ በጉድጓድ ከመጣል ጀምሮ እስር ቤት እስከመወርወር

በሚያደርስ ሁኔታ ውስጥ እግዚአብሔር እንደሠራው የፈለገውን ለመሥራት ለ20 ዓመት መዘጋጀት ነበረበት፡፡ “እግሮቹ በእግር ብረት ደከሙ፥ እርሱም በብረት ውስጥ ገባ” (መዝ. 107፡18) ይላል፡፡ ይህንን ቃል አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜዎች ነፍሱ በብረት እስር ውስጥ ስለመግባቷ ይነግረናል፡፡ ይህም እስር የዮሴፍ ሥጋ በብረት እስር ውስጥ ከመግባቱም በላይ እና ያለፈ ትርጓሜ እንዳለው ጠቋሚ ነው፡፡

እግዚአብሔር ሌላ የሚዘጋጀው ሰው እንደሌለ አድርጎ ነው የሚያዘጋጀን፡፡ በእምነበረድ ቁራጭ ላይ እየሠራ ያለ የቅርጻቅርጽ ባለሙያ በአንድ ወቅት “ምን እየሠራህ ነው?” ተብሎ ተጠይቆ ሲመልስ፣ “ቁርጥራጩ እርግብ እንዳይመስል የሚያደርገውን እክል ሁሉ እየቀረፍኩ፣ እየከተከትኩ እየጣልኩ ነው” ብሎ ነበር፡፡

4ኛ. መከራ እግዚአብሔርን የበለጠ እንድናውቀው ያደርገናል

መከራ ኮሌጅ ገብተን መማር የማንችለውን ትምህርት ያስተምረናል፡፡ ኮሌጅ ወይም ሴሚናርየም ገብተን ባገኘነው ድንቅ ውጤት ምክንያት የሽልማት ወረቀቶች ብዛት ፊታችን ሊከመር ይችላል፤ ዘመን ተሻጋሪ ታላላቅ የሥነ-መለኮት መጻሕፍትንም አብዝተን አንብበን ሊሆን ይችላል፤ ስለመለኮት ባለን አቋምም ድንቅ ድንቅ ነጥቦችን የምናነሳ ሰውም ልንሆን እንችላለን፤ ሆኖም እውቀታችን በአብዛኛው ጽንሰ-ሃሳባዊ ብቻ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ እግዚአብሔርን ለማወቅ ማድረግ የሚገባን አንድ ነገር ነው፤ እርሱን እንደሚገባው ለማወቅ ግን ሌላ ማድረግ የሚገባንም ነገር አለ፡፡ የዘላለም ሕይወት ቁም-ነገር ይህ ነው፡- “እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆነውን እርሱን እግዚአብሔርን፣ የላከውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት” (ዮሐ. 17፡3)፡፡ የሐዋርያውም ጳውሎስ ናፍቆት እና ሩጫው “እርሱን - ክርስቶስን እና የትንሳኤውን ኃይል ለማወቅ ነው” (ፊል. 3፡10)፡፡

ብዙ ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን ከየትኛውም ያለፈ የሕይወት ልምምዳቸው ይልቅ በመከራ ነበልባል ውስጥ እንዳወቁት ይመሰክራሉ፡፡ በዚህ ረገድ ኢዮብ በየትኛውም ዘመን የሚጠቀስ ምሳሌ ነው፡፡ እግዚአብሔርም ስለእርሱ እንዲህ ብሏል፡- “በውኑ ባርያዬን ኢዮብን ተመለከትኸውን? በምድር ላይ እንደ እርሱ ፍጹምና ቅን፥ እግዚአብሔርንም የሚፈራ፥ ከክፋትም የራቀ ሰው የለም…” (ኢዮ. 1፡8)፡፡ በዚህም እግዚአብሔር ከጓጋዎቹ ድሎች አንዱን ለአገልግሎት አቅርቦ አሳይቷል፡፡ ሰይጣን ኢዮብን ለመከራ ዳረገው፡፡ ትክክለኛው ጥያቄ ኢዮብ ምን ዓይነት ሰው ነው የሚለው ነው? እግዚአብሔርን የሚፈራው በከንቱ ነውን (ኢዮ. 1፡9)? ሃይማኖቱ ከራስ ፍላጎት ከመነጨት ሃይማኖቶች እንደ አንዱ መሆን ነው? በመንፈሳዊው ዓለም ስለነበረው ጦርነት ምንም የማያውቀው ኢዮብ ታዲያ እያለፈበት ስለነበረው ብዙ ጥያቄዎች ነበሩት፡፡ አስደናቂው ነገር ደግሞ ለእነዚህ ጥያቄዎቹ ጥርት ያለ ምላሽ አለማግኘቱ ነው፡፡ ከብዙ ጊዜ በኋላ ያገኘው የእግዚአብሔር መገለጥ ግን እርሱን እንደጸጸትና ንስሃ እንዲገባ አድርጎታል፡- “መስማትንስ በጆሮ በመስማት ሰምቼ ነበር፤ አሁን ግን ዓይኔ አየችህ፤ ስለዚህ ራሴን እንቃለሁ፤ በአፈርና በአመድ ላይ ተቀምጬ እጸጸታለሁ” (ኢዮ. 42፡5-6)፡፡

በመከራው ውስጥ እስከናልፍ ድረስ የማንረዳቸው የእግዚአብሔር ቃል ክፍሎች አሉ፡፡ በክርስትና ሕይወት ሠላሳ ዓመታትን ብዘልቅም የኢዮብን መጽሐፍ ተረድቼውም ወደ እርሱ በተለየ መንገድ ተስቤ አንብቤውም አላውቅም ነበር፡፡ በሕይወቴ መከራ እስከመጣ እና የኢዮብን ሕይወት ለመረዳት እስከረዳኝ ድረስ ማለት ነው፡፡ ማርቲን ሉተርም ተመሳሳይ ምስክርነቱን እንዲህ በሚል አባባሉ ይገልጸዋል፡- “መከራ የክርስቲያን ሥነ-መለኮት ትምህርት ቤት ነው፡፡” በመከራ ውስጥ እስካለፍኩ ድረስ የእግዚአብሔርን ቃል ትርጓሜ እንደሚገባው ተገንዝቤ አላውቅም፡፡ መከራዎቼ እና ፈተናዎቼ በሥነ-መለኮት የማስተርስ ዲግሬ የሰጡኝ ብቃቶቼ ናቸው፡፡ “የትኛውም ሰው ቢሆን በመከራ እና በፈተና እስካላለፈ ድረስ የቅዱሳት መጻሕፍትን እውነተኛ ትርጓሜ ማግኘት አይችልም፡፡”

ብዙ መንገድ ስሄድ ከደስታ-ሃሴት ጋር፣

በመንገዴ ሁሉ በወሬ ሰቅዛ ታጫውተኝ ነበር፤

ካጫወተችኝ ግን የቀረልኝ ጥበብ፣

እንደሌለ አየሁ ባሰላስል ባስብ፡፡

ብዙ መንገድ ስሄድ ካዘን-ትካዜ ጋር፣

የተናገረችኝ አንድም ቃል አልነበር፤

የመንገዷ ጓዴ ቃል ካላወጣችው፣

የተማርኩት ጥበብ በእጅጉ ብዙ ነው፡፡

5ኛ. መከራ በሕይወታችን ፍሬን አፍርቶ ለጥቅም ያዘጋጀናል

ዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 15 አማኞችን ከወይን ግንድ ጋር ያነጻጽራል፡፡ ጌታ የወይን ግንድ ነው፤ አባቱ አብ የወይኑ ተንከባካቢ ገበሬ ነው፡፡ አብ ከወይኑ ከቅርንጫፎቹ ፍሬን ይጠብቃል፡፡ እንዲህ ያለው ፍሬም ከክርስቶስ ጋር ካለ ጎብረት እና ከአብ የወይኑ ግርዘት ጋር ይገናኛል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ግርዘቱ ባልታሰበ መንገድ ለውጥ የሚከስት ይሆናል፡፡ የመግረዣ ቢላዎውም የሰላ ሊሆን ይችላል፡፡ የዚህ ሁሉ አጠቃላይ ዓላማም ለእግዚአብሔር ክብር መንፈሳዊ ፍሬ እንዲገኝ ማድረግ ነው፡፡

በምድር ላይ ስማቸው ያልታወቀ፣ ነገር ግን በትህትና የከበሩ እና በመንፈሳዊ ፍሬ የገዘፉ ክርስቲያኖች መኖራቸው ጥርጥር የለውም፡፡ ምናልባትም እነዚህ ሰዎች በዚህ ዓለም ያሳለፉትን መከራ ለሌሎች ማካፈል አልቻሉ ይሆናል፤

ሆኖም የእግዚአብሔር መንግሥት ኃያል ጦረኞች በተደረጉበት በእግዚአብሔር የጸጋው ዙፋን ተጠብቀዋል። ፊሊፕስ ብሩክስ እንዳለው፣ “ነፍሳት በተፈተኑበት ሥፍራ ሁሉ፣ በተራ እና በቀላል መንገድ የመቅደሱን ምሰሶዎች እየጠረበ እያስተካከለ ነው።” ቶማስ ቦስተን በበኩሉ እንዲህ በማለት ያሳስበናል “በመስቀሉ ሥር ካለው ከእግዚአብሔር ፈቃድ አይወጡም፤ በምንም መልኩ እርሱን ከማመን እና በእርሱ ላይ ከመደገፍ እንዲሁም እርዳታውን ከመፈለግ በቃኝ ብለው ወይም አፈንግጠው መውጣት አይቻሉም፤ ይህም እንደመልካም ሥራ በእግዚአብሔር መዝገብ ይመዘገብላቸዋል።”

መከራ አዲስ ዓይነት ፍሬአማነትን ወደ ሕይወታችን ያመጣል። አዲስ ዓይነት የርኅራኄ እና የደግነትን ባሕርይ ሊያጎናጽፈን ይችላል። ይህ በዶክተር ማሪን ሎይድ-ጆንስ ሕይወት የታየ ነው፤ በኋለኛው ሕይወታቸውም ከዚህ ባሕርያቸው ፈቀቅ ብለው አልታዩም። በመከራዎቻቸው ወቅቶች በመከራ ውስጥ ያሉትን ሌሎችን ያስቡ ነበር። በመጨረሻው የሕይወት ዘመናቸውም ልጃችን በጽኑ ታምማ በ13 ዓመት እድሜዋ በሞት ተለየችን። ይህንንም እንደሰሙ በፍጥነት በጣም የሚያጽናና ደብዳቤ ጽፈው ላኩልን። በሦስት ወር ጊዜ ውስጥም እርሳቸውም ወደ ክብራቸው ዕረፍት ሄዱ። ወደኋላ ላይም በአካል ተገኝተው የርኅራኄያቸውን ልብ አሳይተውናል፦ “ታማ ለሞተችው ልጃችን የጸለዩት ጸሎት” ርኅራኄ እና ፍቅር የተሞላው ነው… ለእርሷ፣ ለእናንተ ያለውን ፍቅር እና ርኅራኄ ብቻ ሳይሆን ኃዘናችሁንም አይዘነጉም። የእግዚአብሔር ቤተ ሰዎች አባል መሆን በእውነቱ አስደናቂ እና ክብር የሞላበት ነገር ነው። በእውነት አንዳችን የአንዳችንን ሃሳብና ልብ እንረዳለን።

እኛ ብዙ ጊዜ ኃዘን የእግዚአብሔርን አገልጋዮች ፍሬአልባነት እንደሚጨምር እናስባለን። ቻርለስ ስፐርጅን ግን “እግዚአብሔር ምርጥ ተዋጊዎቹን የሚያገኘው ከመከራ የከፍታ ሥፍራ ነው” ሲል ተናግሯል። ለዚህም ድንቅ ምስክር ሆኖ የሚቀርበው ራሱ እንደሆነም ተናግሯል። ስፐርጅን ሃሳቡን ሲገልጽም እንዲህ ይላል፦

> “የእኔ ተሞክሮ የእግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ተሞክሮ ስለመሆኑ አላውቅም፤ ነገር ግን በምቹ እና ቀለል ባለ የሕይወት ውጣ ውረድ ውስጥ ሆኜ ያገኘኋቸው የእግዚአብሔር ጸጋዎች ግን በመከራ ውስጥ ሆኜ ካገኘኋቸው ጋር ሳነጻጽራቸው ኢምንት ናቸው። በኃዘኔ፣ በሕመሜ እና በመከራዬ ያገኘኋቸው መልካም ነገሮች ተዘርዝረው የሚያልቁ አይደሉም።”

ስለመከራው መንገድ ብዙ የሚያካፍለው ነገር ያለው ቶማስ ቦስተንም በዚሁ ጉዳይ ላይ እንዲህ ብሏል፦ “ባጋጠሙኝ ጠንካራ የመከራ የብረት በሮች የተለመደ ሆኖ ያገኘሁት የእግዚአብሔር አቅርቦት እና በረከት አብሮ መከሰቱ ነው።” ጄ.ሲ. ራይልም በጽሑፍ ባሠፈረው ማገናዘቢያው፣ “መከራ ታላቅ የሕንጻ ንድፍ ጠቢብ ያሰበውን ቅርጽ ለማውጣት እና ከጠንካራ ብረት በብዙ ለመጠቀም ሲፈልግ በእሳት ውስጥ ብዙ እንዲቆይ ማድረጉ እርግጥ ነው፤ እንደዚያ ሲሆን ብረቱ ለሚፈለገው ሥራ በሚፈለገው መንገድ ለመቀረጽ ገር ይሆናል።”

ይህን እውነት በቅዱሳት መጻሕፍትም ሆነ በቤተ ክርስቲያን ድርሳናት ውስጥ ለቁጥር በሚያታክት መልኩ ተጽፎ እናገኘዋለን። እስቲ ስለሐዋርያው ጳውሎስ እና ስለመከራዎቹ እናስብ፤ “የሥጋዬ መውጊያ…ተሰጠኝ፤” ይለናል።

ይህ የተሰጠው መውጊያ የተሰጠበትንም ዓላማ ሲገልጽ፣ “ይኸውም እንዳልታበይ ነው፡፡ …እንግዲህ የክርስቶስ ኃይል ያድርብኝ ዘንድ በብዙ ደስታ በድካሜ ልመካ እወዳለሁ” ብሏል (2ኛ ቆሮ. 12፡7-9)፡፡ ሩዝፎርድ ከአበርዲን በአካል እና በመንፈስ ወደ ብርዱ እንደተገፋ ልናስብ እንችላለን…

“..እንደ ባሕር ወጀብ በማይመች እስሬ

ከጌታዬ ጋራ ቀረሁ ተፋቅሬ…”

በዘመናት ሁሉ እንደታየው በመከራ ውስጥ ለቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ መዓዛ ያለባቸው ደብዳቤዎች ይወርዳሉ፡፡ ስለክርስቶስ ዝም አልልም ብሎ እስር ቤት ስለተወረወረው ጆን ቡንያን እናስብ፤ ጥቅም አልባ - ፍሬ አልባ እንዲሆን በወሕኒ ውስጥ የተዘጋበት መስሎ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ግን በዚያው በወሕኒ ውስጥ አትረፍርፎ እንዲያፈራ አደረገው፤ ይህም “የመናኙ ጉዞ” በሚለው መጽሐፉ ታይቷል፡፡ ቶማስ ቦስተንም በጤና መታወክ ምክንያት መሰቃየቱን እንመልከት፤ እርሱ ብቻ ሳይሆን ልጆቹም በሞት አፋፍ ላይ ደርሰው እያለ ሚስቱ በአእምሮ ጤና ማጣት ትሰቃይ ነበር፤ እንደዚያም ሆኖ አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ውስጥ በቤተ ክርስቲያን አመራር ውስጥ እየተሳተፈ ቢሆንም፣ በቤተ ክርስቲያን አመራሮች ጠብ እየተፈተነ፣ ዋስትና በሌለው ሁኔታ ገቢ የሚያገኝበትን ሥራ እየሠራ፣… ነገር ግን ከዚህ ሰው ሕይወት ከመነገር በሚያልፍ መንገድ ብዙዎች የተባረኩበትን መጽሐፍ ጽፏል፡፡ ስለዚህም ጆን ፍላቨል ይህን አስመልክቶ “አቤት! ከዚህ አሳዛኝ ሁኔታ ውስጥ እንዲህ ያለውን የምሕረት በረከት የሚያውጣው የሰማይ ቀመር ነው!” በማለቱ ልክ ነው፡፡

6ኛ. መከራ እኛን ለክብር ለማዘጋጀት እግዚአብሔርን የእኛን ሁሉ በሁሉ ያደርገዋል

መከራ ወደ እግዚአብሔር ያቀርበናል፡፡ እግዚአብሔር ይፈልገናል በሚል እሳቤ አገልግሎታችንን እንፈጽማለን፡፡ በዚያ ውስጥም እርሱ ለእኛ እንደሚያስፈልገን ፈጥነን እንረዳለን፡፡ ቶማስ ዋትሰን እንዲህ የሚል አባባል አለው፡- “እግዚአብሔር ሰዎችን በጀርባቸው ሲያስተኛቸው፣ ያኔ ወደ ላይ ያያሉ፡፡” እግዚአብሔር እንዲባርከን በለቅሶ እርሱን እንጠራለን፤ ሆኖም እንደውነቱ ከሆነ እርሱን የሚወድ ልብ ሳይኖረን ነው፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር ለእኛ የበረከቶች ሁሉ በረከት መሆኑን ሊያስተምረን ይወድዳል፡፡

በጆን ኒውተን መዝሙር ውስጥ እንደሚስተዋለው፣ “ጸሎት በመስቀሉ መልስ አግኝቷል፡፡” መዝሙሩ እንዲህ ነው የሚለው፡-

“አዎ፣

እየጨመረ እየጨመረ፣ የጭንቄ እሪታ ሲበረታ፣

እንደማይገደው እኔ ስጠፋ፣ እየተናገርኩ “ድረስ!” አልኩ ጌታ፤

እኔ ወጥኜ ያረቀቅኩትን፣ ደንብና ሕጌን መስቀሉ አፍርሶ፣

የመቃብር ደጅ ጠባቂዎቼን ተነሳ ጥሶ፡፡

በእንቅጥቃጤ የለቅሶ ሲቃ “ይህ ለምንድነው?”
“በዚህስ ቃጠሎ ሞቴን ትሻለህ?” ብዬ ስጠራው፣
“ይህ መንገዴ ነው፤ ይሄ ነው መልሴ” ብሎ ቃል ሰጠኝ፤
“ጸጋና እምነት” ጨምር ያልኩትን የጸሎት መልሴን ሊያነናጽፈኝ።

“ባንተ ያሉትን መከራና ጭንቅ አውቃቸዋለሁ፤
ከኩራትና ከራስ ባርነት ነጻ-አውጪ ናቸው፤
በምድር ደስታን ፈላጊነትክን ከእጅህ በማስጣል፣
ላንተ ሁሉ ያለው፣ በእኔ ነውና ለእኔ ይገፉሃል፤
(አይዞህ ይናጡህ እንደ ቅቤ ዋጋ ያስወድዱሃል።)

በመዝሙር ምዕራፍ 73 ላይ አሳፍ ተሰናክሎ ሊወድቅ ትንሽ እንደቀረው ይነግረናል፤ “እኔ ግን እግሮቼ ሊሰናሉ፣ አረማመዴም ሊወድቅ ትንሽ ቀረ” ይላል (መዝ. 73፡2)። ኃጢአተኛው በልጽጎ እያየ እርሱ ግን በአንዳች መኣት እና ቁጣ እንደተመታ፣ እንደተነሳቆለ ነበር። እርሱም ወደ እግዚአብሔር መቅደስ እስከቀረበ ድረስ፣ ግራ ተጋብቶ እና ከራሱ ጋር ተወዛግቦ ተስፋ ቆርጦም ነበር። ወደ እግዚአብሔር በመቅርቡ ግን በውጤቱ ንስሃ ገብቶ እንዲህ አለ፡- “በሰማይ ከአንተ በቀር ምን አለኝ? በምድርስ ከአንተ ውጪ ምን እሻለሁ?” [መዝ. 73፡25 (የግንዛቤ ትርጉም)]። ለዚህ ዘማሪ - ለአሳፍ እግዚአብሔር የሕይወቱ ሁለንተና እና የጥሙ ሁሉ መርኪያ የዘላለም እጣ ክፍሉ ሆኖለታል።

በዚህ መንገድ እግዚአብሔር ለክብር ያዘጋጀናል። ከምኞት እና ከቅንጦት ሕይወት ውጪ መኖር የማንፈልግ ከሆነ፣ ከእግዚአብሔር ያለውን በረከት እንዳለመፈለግ ነው። ማውሪስ ሮበርትስ በጽሑፉ እንደሚለው “እግዚአብሔር ሕዝቡ ወደ ክብር በሚሄደው መንገዳቸው ላይ እንዲቃትቱ እና በለቅሶ ጩኸት እንዲፈልጉት ያደርጋል።” ቶማስ ዋትሰንም ይኸንኑ ሃሳብ አጉልቶ እንዲህ ብሏል፡- “የእግዚአብሔር የምሕረቱ ጽዋ በቀዳሚዎቹ ወራት መከራን ታጠጣለች፤ ከዚያ በኋላ ግን የክብር ወይን ጠጅ ይፈስባታል።”

መ. በጨለማ የወደፊት ዝግጅት አቅርቦት ውስጥ ያለው መጽናናታችን

፲. ከጨለማ አቅርቦት በስተጀርባ ሁልጊዜም የፍቅር ዓላማ አለ

የሕይወት መንገድ አባጣ ጎርባጣ ሲሆን ወይም በላያችን የሚያልፈው የመከራ ማዕበል ሲበረታ አስቸጋሪ የሚሆንብን ነገር ቢኖር እግዚአብሔር በዚያ ሁኔታም ውስጥ ቢሆን እንደሚወደን ማሰብ ነው፡፡ ይህ ልንቀበለው የምንችለው የመጨረሻው ነገር ነው፡፡ ይህ እንዲሰማን ሳይሆን እንድናምነው ነው የተጠራነው፡፡ ሙርዶክ ካምቤል “ኢን ኦል ዜይር አፍሊክሽን” በሚለው መጽሐፉ በሰሜን ስኮትላንድ ስለነበረ አንድ ሚኒስትር ይነግረናል፤ ይህ ሰው በድንገት መንፈሳዊ የሆነች ሚስቱን በሞት አጣ፡፡ በዚያ ምሽት ወዳጆቹ ባሉበት ሲጸልይ እንዲህ አለ፡- “ይህን ከሰማይ የመጣ መላዕክ ቢነግረኝ ባላመንኩ ነበር፤ ነገር ግን ቃልህ እውነት ስለሆነ እና በቃልህም ስለተጻፈ አምነዋለሁ፡፡”

የእግዚአብሔርን ፍቅር መለካት ያለብን በቃሉ እውነት እንጂ በአቅርቦቱ አይደለም፡፡ ሲ.ኤች. ስፐርጅን እንደሚለው “የእግዚአብሔርን የእጁን ስጦታ ማስተዋል በተሳነን ጊዜ፣ እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ልብ በመረዳት እናምነዋለን፡፡” ያለው የወደፊት ዝግጅት አቅርቦት በጨለማ ውስጥ ሲገለጥ ለማንበብ እንቸገራለን፡፡ እንዲህ ባለው ጊዜ ምልከታችን እንዴት ይሁን የሚለውን የሚነገርን ቃሉ ነው፡-

> “በልፍስፍስ ሃሳብ አንፍረድ በጌታ፣
> ይልቅ ጸጋ-ኃይሉን በማመን እንበርታ፤
> ደስ የማያሰኘው አቅርቦት ፈቀቅ ሲል፣
> የፈገግታው ጸዳል ተደብቆ ይታያል፡፡

በእምነት በእግዚአብሔር እጅ ያለውን ሁሉ ማስተዋል ይገባናል፡፡ “ዘ ክሩክ ኢን ዘ ሎት” በተባለው መጽሐፍ የተገለጸው ሁሉ ስለእግዚአብሔር አድራጊነት ነው፡፡ ሁለተኛ ምክንያት ላይ አተኩረን እንቆማለን፡፡ ጥንቃቄ የጎደላቸው ሊሆኑ የሚችሉ ዶክተሮችን እንደመለከታለን፡፡ ቸልተኞች የሆኑ ሾፌሮች ላይ እናተኩራለን፡፡ ሊሆን የሚችለውን በማሰብም ልባችንን በምሬት ልንሞላ እንችላለን፡፡

ዮሴፍ በገዛ ወንድሞቹ እንደዚያ ተዋርዶ እና ተሰቃይቶ ካሳለፈ በኋላ፣ ነገሩን ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ስለመገናኘቱ እንዲህ በማለት ገልጾአል፡- “እናንተ ክፉ ነገርን አሰባችሁብኝ፤ እግዚአብሔር ግን ዛሬ እንደሆነው ብዙ ሕዝብ እንዲድን ለማድረግ ለመልካም አሰበው” (ዘፍ. 50፡20)፡፡ ኢዮብ በሳባውያን ልጆቹን ሲያጣ በከለዳውያን ደግሞ ከብቶቹን፣ ሐብቱን ተነጥቋል፤ በዚህም ሐዘኑ ብዙ ነበር፡፡ ነገር ግን በንግግሩ፡- “እግዚአብሔር ሰጠ፥ እግዚአብሔርም ነሣ፤ የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን”(ኢዮ. ፩፡21) ነበር ያለው፡፡ የእርሱን ሕይወት ጉዳይ

ከእግዚአብሔር ጋር ሲያያዝ፣ ሌሎችን ከመከሰስ ነጻ ሆነ፡፡ ኢዮብም ያደረገው ተመሳሳዩን ነው፡፡ ሳሙኤል ሩዘርፎርድ እንዲህ ብሏል፡-

> “ሃሳባችሁ በግራ-ገብ እና አሳባቢዎች መንደር ውስጥ ውሎ እያደረ ራሳችሁን መስጠት እና በሃይማኖታዊ ታጋሽነት ክበብ ማኖር አይቻላችሁም፤ ከዚያ ይልቅ ሃሳባችሁን ወይ ሰላሜ! ወይ ጊዜ! ይሄ ቢሆን ኖሮ፣ ያ አይሆንም ነበር! በሚል ስትናጡ ትታያላችሁ፡፡”

2. ለብዙ ጥያቄዎች ፈጥኖ ምላሽ ሰጪ አለመኖሩ፣ ምስጢራዊ ሆኖ ይዘልቃል

የነገሩ ዋና ነገር የተመሠረተው በዚህ ወሳኝ ጉዳይ ላይ ነው፡፡ እንግዳ የሆነ አያዎ (አይ-አዎ) ሊመስል ይችላል፤ ነገር ግን ኢዮብ ይህ እንዳይገባው ፈቃደኛ በሆነ ጊዜ ነው ነገሩ ሊገባው የጀመረው፡፡

> “ታምራቱን ሊያደርግ እግዚአብሔር ይሠራል፤
> መንገዱ ረቂቅ ነው በምሥጢር ይሄዳል፡፡
> ዱካውን ባሕር ላይ ከኋላው ይተዋል፤
> ወጀቡን ተራምዶ ካሰበው ይደርሳል፡፡
>
> እጅግ በጠለቀው በክሕሎቱ ምጥቀት፣
> ረቂቅ ንድፍ ነድፎ በብርሃን ስሪት፣
> ይጠብቃቸዋል እንደ ቃል እንደ ጌጥ፣
> የልዑል ፈቃዱን በሥራው ለመግለጥ፡፡

ይህ እንደዚህ የማይሆነው ለምንድነው? እግዚአብሔር እግዚአብሔር ነው፤ ሰው ደግሞ ሰው፡፡ ይህም የእግዚአብሔርን ታላቅነት በመጠበቅ የሚገለጥ ነው፡፡ በዮሐንስ ወንጌል 13፡7 ላይ ተመሥርቶ ራልፍ ኤርኪን “የጨለማው የዝግጅት አቅርቦት በጊዜው ፍንትው ብሎ ይገለጣል” በሚል ርዕስ በሰበከው ስብከቱ በጨለማ የዝግጅት አቅርቦት ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔርን ዓላማ ያብራራል፤

> ራሱን እርሱ በሚፈልገው እና በሚመቸው መልክ የራሱን መልክ እና የከበረ ፍጽምና በእኛ ውስጥ ለማግኘት እንዲሁም ሃሳቡ ከሃሳባችን መንገዱም ከመንገዳችን እንደሚለያይ ለማረጋገጥ ነው፡፡ እንደእኛ ሃሳብ እና ምኞት የሚሠራ ከሆነ እንደፈቃዱ የሚሠራ ልዑላዊው እግዚአብሔር እርሱ እንደምን ጂሆቫ ይሆናል?

እግዚአብሔር ለእኛ የማብራራት ግዴታ የለብንም፡፡ እኛ በውስጠ ታዋቂነት እርሱን የማመን እና የመታዘዝ ግዴታ አለብን፡፡ በኢዮብ ሕይወት እንደታየው እግዚአብሔር ዝም ባለበት ሁኔታ እርሱን ማመን ይከብዳል፤ ነገር ግን እርሱን ልናምነው ይገባል፡፡

በመከራ ውስጥ የእግዚአብሔርን ዝምታ ችግር ዶክተር ሮናልድ ደን እንደሚከተለው ጥበብ በተሞሉ ቃላት ገልጸውታል፡-

> “እንደሚመስለኝ ይህ ከሁሉም አስቸጋሪው ክፍል ነው፡፡ ለምን እንደሆነ ካወቃችሁ ሁሉኑም ነገር መውሰድ ትችላላችሁ፡፡ የትም ቦታ ስሄድ፣ በሁሉም ስብሰባዎች ለምን? የሚል ጥያቄ እጠየቃለሁ፡፡ … አንድ ነገር ልንገራችሁ፡- እግዚአብሔር በጣም አልፎ አልፎ ካልሆነ ለምን የሚል ጥያቄያችሁን አይመልስም፡፡ ጥያቄአችሁ መልስ ስለሌለው አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ ምናልባትም እናንተ እና እኔ ነን የእግዚአብሔርን ምላሽ ላንረዳው የምንችለው፡፡ ከዚያ በተጨማሪ ግን እየሆነ ያለው ለምን እየሆነ እንዳለ ባንረዳም እንኳን እግዚአብሔርን ማመን መማር አለብን፡፡ እግዚአብሔርን ጥያቄዎችን እንጠይቀዋልን፤ ብዙ ጊዜም የምንጠይቀው “(እግዚአብሔርን በእኛ ሁኔታ ከትተን) ጌታ ሆይ ራስን ግለጥልኝ” ብለን ነው (ዎኪንግ ዊዝ ዘ ኪንግ፣ ገጽ 173)፡፡

“ለምን ይሄ በእኔ ሆነ?” ርዕሶችን የያዙ እና እንዲህ ለሚሉ ሁሉ መልሶችን እንደያዙ የሚለፍፉ መጻሕፍት በእጅጉ ተወዳጅ በመሆናቸው ምክንያት፣ በተነባቢ ደረጃቸው ከፍተኛ ሥፍራን ተቆናጠው ይታያሉ፡፡ በተለይም በአሜሪካ ክርስቲያን አንባቢዎች ዘንድ ራቢ ሃሮልድ ኩሽነር “ዌን ባድ ቲንግስ ሃፕን ቶ ጉድ ፒፕል - ክፉ ነገር በበጎ ሰዎች ላይ ሲሆን” በሚል ርዕስ የጻፈው መጽሐፍ የአንባቢን ትኩረት እና ይሁንታን በእጅጉ አግኝቷል፡፡ ምክንያቱም መጽሐፉ ለመከራ ችግሮች መልስ ይሰጣል፡- እግዚአብሔር ውስን ነው፤ እግዚአብሔር ሰዎች በሕይወት ማግኘት ያለባቸውን ሁሉ እንዲያገኙ እና መድረስ ያለባቸው ሥፍራ እንዲደርሱ ይፈልጋል፤ ነገር ግን አቅሙ ውስን ነው፡፡ ለዚህ ምላሽ የሚሆነውን ፈጥኖ የጻፈው “ለምን በእኛ እንዲህ ሆነ?” በሚል ርእስ “በእግዚአብሔር ሰዎች ላይ ክፉ ነገር ሲሆን” በሚል ንዑስ ርዕስ ዋረን ዊርስቤ የተባለ ጸሐፊ ነው፡፡

ዊርስቤ በመጽሐፉ ከኢዮብ መከራም እንድናስተውል የጠቀሰውም ጉዳይ እንዲህ ይነበባል፡-

> እግዚአብሔር ኢዮብ በለቅሶ እየጠራው ባለ ጊዜ ጥያቄዎቹን ፈጥኖ ያልመለሰበት አንዱ ምክንያት ከኢዮብ ጋር ያለውን የአምላክ-ሰው ግንኙነት በጸጋው ማስቀጠል ስለፈለገ ነው፡፡ ኢዮብ ከሰማይ ጋር በውል የተመሠረተ “የተሸቀጠ እምነት” እንዲኖረው እግዚአብሔር አልፈለገም፡፡ እንዲኖረው የፈለገው እምነት በፍቅር፣ በምሕረት፣ በጸጋ፣ በበጎነት፣ በርህራሔ ላይ የተመሠረተ እና በዚህ ግንኙነታቸው መካከል ምንም ዓይነት እክል የማይገባበትን ነው፡፡ “ጻድቃን ለምን በመከራ ውስጥ ያልፋሉ?” … “የእኛን መከራ እንደተገቢ የሚያየውንስ እግዚአብሔርን ማምለክስ አለብን?”

3. ብቸኛው ጥቅል መልስ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ቅርበት ማጎልበት ነው

ስለመከራችን ከሚሰጥ ማንኛውም ማብራሪያ ይልቅ፣ ወደ እግዚአብሔር መቅረባችን በእጅጉ የበለጠ ጠቀሜታ ያለው ልምምድ ነው፤ “እግዚአብሔርን ልጠይቀው የምፈልገው ጎልቁ መሣፍርት የሌላቸው ጥያቄዎች ነበሩኝ፤ እርሱን እንደሚገባው ስቀርበው ግን ጥያቄዎቼ ሁሉ እንደጉም በንነው እንደምናምን

ሆነው አገኘኋቸው” (ክርስቶፈር ሞርሌይ)። ነገሮችን በዚህ መንገድ ብቻ ነው ማየት ያለብን። በዘማሪው አሳፍ ሕይወትም የሆነው እንዲህ ነው። አሳፍ እንደተቀጣ ሆኖ በስቃይ ራሱን እያየ ኃጢአተኞችን ተደላድለው የብልጽግናን ኑሮ ሲኖሩ ማየት ለእርሱ እጅግ የሚያም ሁኔት ነበር፤ ይህ የሆነው ግን ወደ እግዚአብሔር መቅደስ እስከቀረበ እና ወደ እግዚአብሔር መገኘት ውስጥ እስከገባ ድረስ ብቻ ነው። በዚያ አሳፍ የእግዚብሔርን ቃል ሰማ። ከዚያም እንዲህ አለ “ፍጻሜያቸውን አስተዋልኩ” (መዝ. 73፡17)። በዚያ ዝም ብሎ ደስታ አይደለም የተሰማው፤ ይልቁንም መረዳትን ነው ያገኘው።”

ቶማስ ቦስተን ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት የማድረግን አቅርቦተ-ዝግጅት አስመልክቶ ይናገራል። አቅርቦተ-ዝግጅት የሚለውን ቃል እንደ ቶማስ አባባል የሚፈታው የሚተረጉመው ቃሉ ነው። አቅርቦተ-ዝግጅት በሕይወቴ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚተገብር የመስክ ሠራተኛ ነው። ዘማሪው በነበረበት ሁኔታ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውን ግንኙነት አቋርጦ ነበረ። ነገሮችን ይመለከት የነበረው በትክክለኛው መነጽር እና የእይታ አቅጣጫ አልነበረም። ስለዚህም “በአንተ ዘንድም እንደ እንስሳ ሆንኩ” ብሎ የነበረበትን ሁኔታ ይገልጸዋል። ትክክለኛውን የእይታ አቅጣጫ ሲያገኝ ደግሞ “ለእኔ ግን ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይሻለኛል” ብሏል።

ሁኔታችን ምንም ዓይነት ይሁን፣ ኃላፊነታችን በአገልግሎታችን መንገድ ላይ ያለመነቃነቅ መሄድ ነው፡-

“ተደላድለህ ቆመህ በእግዚአብሔር እምነትህ
መንገድህን ቀጥል፣ ቀጥል በተግባርህ።”

ብዙ ጊዜ ሰዎች መከራ ውስጥ ሲገቡ በዚያ ውስጥ ያለውን የእግዚብሔርን ፈቃድ ዓላማ ከመረዳት ይልቅ ችግሩን ለማጥፋት በብዙ ይጨነቃሉ። ማቲው ሄነሪ እንደሚለው ግን “መከራ ሥራውን እስኪጨርስ እንጂ ከዚያ በኋላ ደብዛው አይገኝም።” መከራ ለእኛ የተቀደሰ እንዲሆንም መጸለይ የሚገባን እኛው ነን። ዋረን ዊርስቤ “ዋይ አስ - ለምን በእኛ ላይ ሆነ?” በሚለው መጽሐፉ ራሱን በችግሮች ባሕር ውስጥ ስላገኘ ጓደኛው ያወጋናል። ይህችን በመከራ ባሕር የተገኘች ጓደኛውን ለማጽናናት እና ለማበረታታት አንድ ቀን እንዲህ አላት፡- “ለአንቺ ምን እንደምንጸልይልሽ እንድታውቂ እፈልጋለሁ።” እርሷም “ይህ የሚደነቅ ሃሳብ ነው፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ምን እንዲያደርግ ነው የምትጸልየው?” በማለት ጠየቀችው። ዊርስቤም ይህን መልስ ለመመለስ ሲያመነታ ቆይቶ የተወሰኑ ሃሳቦቹን አካፈላት። እርሷም ስለሃሳቡ አመስግና “በዚህ መከራ ካለፈኩ በኋላ እንዳልከስር ጨምረህ ጸልይልኝ” አለቸው።

4. ውጤቱ ከምሕረት ጋር ብዙ መሆኑን ማረጋገጫውን ማግኘት እንችላለን

ራልፍ ኢርስኪን እንደሚለው “ክርስቶስ ለሕዝቡ የሚሠራው እያንዳንዱ ሥራ ልንረዳው ከምንችለው ጊዜ ይልቅ በውስጡ የበለጠ ታላቅ እና የከበረ ነገር አለው።” ዊሊያም ኮፐርም በታወቀ አገላለጹ ተመሳሳይ ሃሳብ አስተላልፏል፡-

“እናንተ የፈራችሁ ቅዱሳን አይሉ፣
ደመናው አረገዘ ጠቆረ አትበሉ፤
ደመናው ያረገዘው ምሕረት ይገለጣል፤
ባናታችሁ ሲሳይ በረከት ይፈሳል።

ቀን በቀን ሲተካ ያለውን አዝሎ፣
ዓላማው ሳይዘገይ ስለሚታይ በስሎ፣
ልባችሁ አይውደቅ በመከራ ዝሎ፤
የቀናችሁ እንቡጥ መራራ ቢመስልም፣
ከአበባው በስቲያ ግን ጣፋጭ ብስሉ አይቀርም።”

ይህንን አዘውትረን በእግዚአብሔር ቅዱሳን ሕይወት ውስጥ እንመለከተዋለን። ዮሴፍን እና የመከራውን ረጅም ዓመታት አስቡት። እሥር ቤት እና ቤተ መንግሥት ሊነጻጸሩ የሚችሉት እንደት ነው! “እግሮቹም በእግር ብረት ደከሙ፥ እርሱም በብረት ውስጥ ገባ። ቃሉ እስኪመጣለት ድረስ፥ የእግዚአብሔር ቃል ፈተነው። ንጉሥ ላከ ፈታውም፥ የአሕዛብም አለቃ አስፈታው። የቤቱ ጌታ፥ የጥሪቱ ሁሉ ገዢ አደረገው፥ አለቆቹን እንደ ፈቃዱ ይገሥጽ ዘንድ፥ ሽማግሌዎቹንም ጥበበኞች ያደርጋቸው ዘንድ” (መዝ. 105፡18-22)። የእግዚአብሔ የዝግጅት አቅርቦት ጊዜ አንዳንድ ጊዜ አስደናቂ ሆኖ ይታያል። በወቅት የሚገለጠው የምሕረቱ አመጣጥ እንዲህ ያለውን ጊዜ ዋጋውን ከፍ ያደርገዋል። የእግዚአብሔር የዝግጅት አቅርቦት እንዲህ ያለውን ባቡር ስቦ እየሳበ ያመጣና የነገሩን ውጤት ደስታ በደስታ ያደርገዋል።

አሁን ወይም በመከራ ጊዜ ያለውን የእግዚአብሔርን የዝግጅት አቅርቦት አሥራር ላንረዳው እንችላለን፤ እርሱ ግን የሚሠራው ከፍ ባለ ደረጃ ነው። ኢዮብ እግዚአብሔር እና ሰይጣን በእርሱ ላይ እንደወራረዱ እና በሕይወቱም ጦርነት እንደተከፈተ የተረዳው ምንም ነገር አልነበረም። እግዚአብሔር የጸጋውን አሸናፊነት ለመግለጥ ተሰይሟል። ኢዮብ ግን ሕይወቱን እንደምናምን - እንደተራ እቆጠረ መጥቷል። ሁሉን እንዳጣ እና ምንም እንዳልቀረው በተረዳበት በዚያ ቅጽበት ካደረገው ነገር ሁሉ ታላቅ የሆነውን ነገር አድርጓል፡- እግዚአብሔርን ሲያመሰግን የሰይጣንን ውሸት እየተናገረ ነበር። ዮሴፍ ወደ ጉድጓድ ከተወረወረ ከሃያ ሁለት ዓመታት በኋላ ነው ለምን እንደተጣለ ያወቀው።

ቶማስ ቦስተንም በኢትሪክ የመከራ ማዕበል ውስጥ ከመግባቱ ጀርባ ያለውን ዓላማ ሊረዳው አልቻለም ነበር። በየዕለቱም የእግዚአብሔርን አቅርቦተ-ዝግጅት እንዴት እንደሚያስናግድ በመለማመድ አሳልፏል። ይህም በእያንዳንዱ የትውስታው ገጾች ላይ ተከትቦ ይገኛል። ብዙዎች ራሱን በመከራ ውስጥ ለማሳለፍ የተወሰነበት ዓይነት እንግዳ ሰው አድርገው ደምድመው ሊሆን ይችላል። በምንም ዓይነት ጥልቅ እና ረጅም የሐዘን ድባብ ውስጥ ይለፍ እንጂ፣ እርሱ መንፈሳዊውን ነገር በጥልቀት የተለማመደ ጻድቅ ሰው ነው። የተፈራረቀበት የመከራ

መዓት በእርግጠኝነት በኋላ ላይ ያፈራው የተትረፈረፈ ፍሬ ምንነት እና ለምን ሆነ የሚሉ ጥያቄዎች በድካሙ የሠራው ሥራ ማብራሪያ መልስ ነው፡፡ በእርሱ ዘመን በቤተ ክርስቲያን የታወቀውን ሥፍራ ይዘው የነበሩ ሰዎች ተረስተው፣ የእርሱ የቦስተን የጽሑፍ ሥራዎች ግን ዛሬም ድረስ በመላው ዓለም ተነባቢ ናቸው፡፡

ሕይወታችን በክር የሚሠራን የጥበብ ሥራን ይመስላል፤ ከጀርባው ብዙም ትርጉም የማይሰጡ ንብርብር ባለ-ብዙ ቀለም ክሮች ተጠላልፈው ትርጉም የማይሰጡ መስለው ሲታዩ፣ ከፊት ግን ውብ ገጽታ ያለውን አንዳች ምስል ያሳያሉ፡፡

“የሸማኔው መወርወሪያ ድምጹን እስከሚያቆም፣
መዘወሪያው የዙረቱን ሩጫ ገቶ እስከማይደግም፣

እግዜር የሸራውን ፊት-ለፊት እስኪያሳየው፣

ምን ሠርቶ እንደቆየ እርሱው እስኪገልጠው፣

ጥቁሩን የዳንቴል ክር እንዴት እንደሠራው፣

በሸማኔው ክሕሎት እንዴት እንዳስዋበው፣

ልክ እንደ ወርቃማ እንደ ሐምራዊው ክር፣

በእቅዱ ዝዋሪ ተሠርቶ እስከሚያምር፣

ማን ያውቃል መንገዱን? ማነው የሚመረምር?

የነገርን ሁሉ ፍጻሜ በሚገባ መመልከት አለብን፡፡ “እነሆ፥ በትዕግሥት የጸኑትን ብፁዓን እንላቸዋለን፤ ኢዮብ እንደ ታገሠ ሰምታችኋል፥ ጌታም እንደ ፈጸመለት አይታችኋል፤ ጌታ እጅግ የሚምር የሚራራም ነውና።” (ያዕ. 5፡11)

መደምደሚያ

እግዚአብሔር መከራን እና ክብርን እንዳይነጣጠሉ አድርጎ አጣምሯቸዋል። ክርስቶስም የሄደው በዚሁ መንገድ ነው። እርሱ እንደ አዳኛችን ፍጹም የሆነው "በመከራ ውስጥ" ነው። መከራን ታግሷል። ኃጢአት ግን አልተገኘበትም።

የመከራ መንገድ ኃጢአተኞችን ወደ ክብር እና ወደ ፍጽምና የሚውሰድ አንዱ ክፍል ስለመሆኑ ከዚህ በላይ ምን ማለት ይቻላል! ከመከራችን ጋር ለመታረቅስ እጅግ ብዙ ማስረጃዎች አልቀረቡም ወይ! ሮበርት ሙሬይ ማኬይኒ እንዲህ ብሏል፦ "ሁልጊዜም ከእግዚአብሔር ዘንድ ያለችው የመከራ እጅ በጣም እንደምታስፈልገኝ ትሰማኛለች።" ሩዝፎርድ በበኩሉ "ስለመዶሻው፣ ስለመጥረቢያው እና ስለማቅለጫ እሳቱ እግዚአብሔር ይመስገን፤" በተመሳሳይ ሲ.ኤች. ስፐርጅንም እንዲህ ብሎ ጽፏል፦ "ይህ በእሳት የመቅለጫ ክፍል ነው፤ *መዳመጫ* እና በመዶሻ *መቀጥቀጫም* ነው።"

በዘመናችን ባለው ክርስቲያዊ አመለካከት ችግሮቻችንን፣ ሕመማችንን፣ እንዳንሸወድ እንጠንቀቅ፤ አብረን እንድንከብር አብረን መከራን እንቀበላለን። ያለ መከራ ክብር የለም፦

ሲንኪሌር ፈርጉሰን "በእምነታችሁ ላይ ጨምሩ" በሚል ርዕስ በጻፉት ጽሑፍ በአንድ ቤተ ክርስቲያን የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ተለጥፎ ያየውን ነገር ያሳታውሳል፤ እንዲህ ይላል፦

ወደ ውስጥ - የሥራ ክፍሉ

ፎቅ ላይ - የሥራ ውጤት ማሳያ ክፍሉ

በምድር ያለው ሕይወታችን የሥራ ክፍላችንን ይመስላል። እኛ የተግባር መስኮች ነን። ሕይወቱ የእግዚአብሔር መሮ አለበት። በአማርኛ "ባሕርይ" የሚል ፍቺያለው የእንግሊዝኛው ቃል "ካራክተር" ምንጩ የግሪክ ቃል ሲሆን በጠንካራ ሥፍራ ላይ ምስል እና ቅርጽ ለማውጣት መቆርቆር፣ መፈቅፈቅ እና ማሸት የሚል ትርጓሜ አለው። የሕይወታችን መከራዎች እግዚአብሔር የልጁን ባሕርይ ለመቅረጽ እና መልኩን ለማውጣት በእኛ ልብ ላይ ለመቅረጽ የሚቆረቁርበት፣ የሚፈቀፍቅበት እና የሚያሸበት መሣሪያዎች ናቸው። በመከራ ውስጥ ማለፍ አስደሳች አይደለም፤ ነገር ግን ደግሞ አትራፊ ነው። ፎቅ ላይ - በላይ በሰማይ ያለቀው የእግዚአብሔር የሥራ ውጤት ማሳያ ነው። ያም የልጁ ውብ መልክ ነው።

የእግዚአብሔር ሰዎች በከንቱ በፍጹም ዋጋ አይከፍሉም። ዛሬ-አሁን የምንከፍለው ዋጋ ሁሉ ወደፊት የክብር ክፍያ አለው። የአሁኑ-የዛሬው መከራዎቻችን ከምናገኘው ክብር ጋር ሲነጻጸሩ ምንም ናቸው - እዚህ ግቡ የሚባሉ አይደሉም። ማኬይን እንደሚለው "ከኃጢአት በቀር በታሪካችሁ ያለፈው የእያንዳንዱን ክስተት ውጤት ፈጥኖ ታዩታላችሁ። እያንዳንዱ የችግር ማዕበል ኃጢአት ወደሌለበት ብሩህ የጸሐይ ጸዳል ወደሚያንጸባርቀው ዘላለማዊው የባሕር ዳርቻ እየገፋችሁ ነው።

“በሕይወቴ ያለፈው የውቂያኖስ ወጀብ፣
የእሾኻማው መንገድ ወግቶ የሚያንገበግብ፣
የመካራው ናዳ፣ ያ ሁሉ የሞት ድባብ፣
ትላንቶቼ ናቸው ስንቄ ለነገዬ፣
ቅኝቶቼም ናቸው ግጥም ዝማሬዬ።።

አውቃለሁ ይፈሳል፣ የበረከቱ ቀንድ ከላይ ከላዕላይ፣
የምድሬን ዋይታ፣ የምሬትን ክረምት ገፎ ሊያደርግ ጸደይ፤
ያንን ምድረ-በዳ በለምለም ሊሞላው ሊያንጸባርቅ ሰማይ፣
በኤደን አበቦች ምድር ውበት ስታይ።።